ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

ህዳር 2013 የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች ቁጥር 37

# የገጠር መሬት ይዞታ በኢትዮጵያ - አጠቃላይ ግምገማ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል።

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን።

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org

## የመሬት ይዞታ በንጉሳዊው ዘመን

በኢትዮጵያ በ1950ዎቹ እና 1960ዎቹ በነበረው የተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ የመሬት ባለቤትነት መብት፣ የገበሬዎች በመሬት ከበርቴዎች ጥገኝነት ስር መውደቅና የመሬት ስሪት ለውጥ አስፈላጊነት ዋና ቁልፍ ጉዳዮች ነበሩ። በ1961 ዓ.ም በአዲስ አበባ ‹‹መሬት ላራሹ›› በሚል መፈክር ስር የተደረገው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ የዚህ ንቅናቄ ከፍተኛ አካል ነበር። በወቅቱ የነበረው የመሬት ይዞታ ስርዓት ኢ-ፍትሀዊ፣ በዝባዥ፣ ለኢኮኖሚ ልማት እንቅፋት እና የፊውዳል ስርዓት ዋና ምሰሶ እንደሆነ በተማሪዎች ንቅናቄ እና በመንግስትና በግል ዘርፍ በተሰማሩ ተራማጅ ሠራተኞች መካከል ሰፊ መግባባት ላይ ተደርሶ ነበር። ስርዓቱ በአመዛኙ በገባር ላይ የተመሠረተና በመሬቱ ላይ የሚሰራው ገባርና ጪሠኛ ላይ ከፍተኛ በደል የሚያደርስ ነበር።

በወቅቱ የነበረው የመሬት ይዞታ አወቃቀር ስርዓት ውስጥ የነበሩት ዋና ዋና የመሬት ይዞታዎች የሚከተሉት ነበሩ፡-

- ✓ መሬቱ ባለበት አካባቢ በማይኖሩ በአብዛኛው መሣፍንት በሆኑ በባለቤትነት የተያዙና በገባሮችና ጪሰኞች የሚታረሱ ሰፋፊ መሬቶች፤
- ✓ በየአካባቢው በሚገኙ ባላባቶች የተያዙና በገባሮችና ጪሠኞች የሚታረሱ ሰፋፊ መሬቶች፤
- ✓ ከአገሪቱ ጠቅላላ መሬት አንድ ሦስተኛ እንደሚሆን የሚገመትና በመንግስት እጅ የነበረ መሬትና እና
- ✓ በሠሜንና በማዕከላዊ የሀገሪቱ ክፍሎች በአነስተኛ ገበሬዎች የተያዙ አነስተኛ መሬቶች ነበሩ።

በፅንፈኛ (radicals ) እና ተራማጅ ኃይሎች እንዲሰፍን ይታገሉለት የነበረው የመሬት ማሻሻያ በርካታ ግቦች ነበሩት። ከነዚህም መካከል የነበረውን ስርዓት ስህተቶች ማስወገድ፣ለተጨቆኑ አርሶ አደሮች ፍትህ መስጠት እና የሀገሪቱን ፖለቲካ ማዘመን በዋነት ይጠቀሳሉ። በአንፃሩ የንጉሳዊው መንግስት የመሬት ስርዓት ለውጦችን የማይቀበል ከመሆኑም በላይ ንጉሠ ነገሥቱ ከዙፋናቸው ያወረዳቸው ወታደራዊ አመፅ ዋዜማ በመሬት ከበርቴውና በገባሩ/ጪሠኛ መካከል ያለውን ግንኙነት በሕግ ለመገደብ የቀረበውን ሀሳብ በመሣፍንቶች ጠንካራ ግፊት ወደ ጎን ትተውታል።

## የደርግ የመሬት ሪፎርም

ደርግ የተሰኙትና አብዮቱን የመሩት መካከለኛና የበታች መኮንኖች ስብስብ አረጋዊውን ንጉሠነገሥት ከስልጣን

በማውረድ በመስከረም 1966 ዓ.ም በትረ ስልጣኑን ተቆጣጠሩት:: ከስድስት ወራት በኋላ በመጋቢት 1966 ዓ.ም ስርነቀል እና ሁሉን አቀፍ የሆነ የመሬት ማሻሻያ አዋጅ ወጣ:: ይህንንም ተከትሎ በአዲስ አበባ እና በሌሎች ከተሞች ከፍተኛ የድጋፍ ሰልፎች ተካሄዱ:: ሰልፉ ለመሬት አዋጁና በዚህም ከመሬት ከበርቴው ላይ መሬቱን ካለምንም ካሣ የመውሰዱ ሂደት ህዝባዊ አዎንታዊ ድጋፍ እንዳለው በግልፅ ያሳየ ነበር::

የመሬት አዋጁ ቁልፍ ድንጋጌዎች የሚከተሉት ነበሩ፡-

- የግል መሬት ባለቤትነትን ማስወገድና በተቃራኒው መሬትን በህዝብ ባለቤትነት ስር እንዲሆን ማድረግ፣
- ገበሬዎች ለሚያርሱት መሬት የመጠቀም መብት መስጠት፣
- መሬትን በሽያጭ፣ በኪራይ፣ በሊዝ፣ በብድር ወይም በውርስ ማስተላለፍን መከልከል፣
- ጪሠኝነትን ማስወገድ እና እርሻ በባለቤቱ ብቻ እንዲካሄድ የእርሻ ቅጥር ስራን ማስቀረት ያካትታል::

የመሬት ማሻሻያውን ተግባራዊ ለማድረግና እንዲሁም የአካባቢው ወኪል አስተዳዳሪዎች ሆነው እንዲያገለግሉ የገበሬ ማህበራት እንዲቋቋሙ ተደርጓል:: የመሬት አዋጁ በመጀመሪያ በእድገት በሕብረት ዘማቾች በኋላም ደጋፊና ወገንተኛ በሆኑ የደርግ የፖለቲካ ካድሬዎች አመራር ተፅዕኖ በዓመታት ውስጥ ተግባራዊ ተደርጓል::

ይሁን እንጂ የመሬት አዋጁ ስር ነቀል ለውጥ ቢያመጣም ድክመቶቹ የታዩት ብዙም ሳይቆይ ነበር:: ዋናው ድክመት በየጊዜው ይደረግ የነበረው የመሬት ድልድል እና በዚህ ሳቢያ የተከተለው የይዞታ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ መቀነስ ሲሆን፤አዋጁ ከስነ-ህዝብ ጋር የተያያዙ ለውጦችን ግምት ውስጥ ያስገባ ባለመሆኑ መሬት አልባነት አሳሳቢ ስጋት ሆኖ ብቅ አለ:: ከዚህ በተጨማሪ የእርሻ ቅጥር ስራ፣ የመሬት ኪራይ እና ሌሎች ተመሳሳይ ልማዳዊ የመሬት ማስተላለፍ አሰራሮች መከልከል የስራ አጥነትን ከማስከተሉ ባሻገር የመሬት ሀብትን ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም እንዳይቻል አደረገ:: እንዲሁም የደርግ መንግስት ካለበቂ ጥናት በችኮላ ተግባራዊ ሊያደርግ የሞከረው የሶሻሊስት ግብርና ስርዓት፣ በ1970ዎቹ የጀመረው የሠፈራ ፕሮግራም እና የሠብል ዋጋ ተመን ቁጥጥር ቀደም ሲል የመሬት ድልድሉን በአድናቆት በተቀበሉት ገበሬዎች ዘንድ ቅሬታ አስከተለ::

የሶሻሊስት ግብርና ስርዓት ፕሮግራም በአንድ በኩል ገበሬዎች መሬቶቻቸውን በአንድ ላይ በማድረግ በጋራ የሚያመርቱባቸውን የገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበራትን በማቋቋምና በማጠናከር ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ በሌላ በኩል የመንግስት እርሻዎችን በማቋቋም ላይ የተመሠረተ ነበር:: በዚህ ሂደት ውስጥ ውጤታማ ያልነበሩት፤ ብክነትና ብልሹ አሰራር የተንሰራፋባቸው የመንግስት እርሻዎች ሰፊ ለሆነ የደን ሀብት መጨፍጨፍና ለአያሌ ለአርሶ አደሮች ከመሬቶቻቸው መፈናቀል ምክንያት ሆነዋል::

በእነዚህ ፖሊሲዎች እና በመጥፎ አፈፃፀማቸው ምክንያት የመሬት አዋጁን ተከትሎ እየጨመረ መጥቶ የነበረው የሰብል ምርት በ1970ዎቹ መጨረሻና በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ እያሽቆለቆለ ሄደ:: በ1977 የተከሰተው አሰቃቂ ረሀብ የገበሬዎችን ቅሬታና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣውን የግብርና ምርት ቀውስ ተከትሎ የተከሰተ ነው:: በአጭሩ ስር ነቀል ተብሎ የነበረው የመሬት ማሻሻያ ግቦቹን ያላሳካ ሲሆን ይባስ ብሎም አርሶ አደሮች እጅግ ይፈልጉት የነበረውን የመሬት ዋስትና ሊያስገኝላቸው አልቻለም::

## የድህረ ደርግ ማሻሻያዎች

በ1983 ዓ.ም ደርግን የተካው ኢህአዲግ መራሹ መንግስት የደርግን የመሬት አዋጅ ድንጋጌዎች በአብዛኛው የተቀበለ ሲሆን የተወሰኑት ላይ ማሻሻያ አድርጓል:: የ1987 ህገ-መንግስትና ተከትለው የወጡት የ1989 እና 1997 የመሬት ህጎች መሬትን በውርስ የማስተላለፍ መብት የሚሰጡ ሲሆን፣መሬት ማከራየትና በራስ መሬት ላይ የቅጥር ጉልበት መጠቀምን ይፈቅዳሉ:: የመሬት አስተዳደር በተመለከተ በአዲሱ የፌዴራል የፖለቲካ ስርዓት አወቃቀር መሠረት የፌዴራሉ መንግስት ሰፊ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን የማስቀመጥ ሚና በህግ የተሰጠው ሲሆን፤ የመሬት አስተዳደሩ ስራ ደግሞ ለክልሎች የተሰጠ ኃላፊነት ሆኖ ተከፋፍሏል:: ሆኖም ግን የክልል ህጎች ከፌዴራል ህጎች እና ከህገ-መንግስቱ ጋር የሚስማሙ መሆን እንዳለባቸውም ተደንግጓል::

አዲስ የወጡት የመሬት ህጎች አንዱ ዋና ዓላማ ለመሬት ባለይዞታዎች የይዞታ ባለቤትነት ዋስትና መስጠት ሲሆን፤ በዚህ ረገድ በ1997 በወጣው የፌዴራል የመሬት ህግ ውስጥ የገበሬዎችን የመሬት ባለቤትነት መብትን ማረጋገጥ ዓላማው ያደረገ የመሬት ምዝገባ እና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት ድንጋጌ መካተቱ አዲስ እርምጃ ነው፡፡ በዚህም የመጀመሪያ ደረጃ የመሬት ምዝገባና ሠርተፊኬት ማረጋገጫም ከ1994-1998 ባሉት ዓመታት ተካሄዷል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ምዝገባና ሠርተፊኬት በገበሬዎች በራሳቸው እንዲካሄድ በመደረጉ በአነስተኛ ወጪና በአጭር ጊዜ ውስጥ ቢከናወንም፤ሂደቱ የተለያዩ ስህተቶች የታዩበት ነበር፡፡ መሬቶቹ በልማዳዊ የልኬት ዘዴና መንገድ መለካታቸውና መጠናቸው ትክክለኛ አለመሆን፤ የእርሻ ማሣ ወሰኖች በተንቀሳቃሽ ነገሮች ላይ መመስረታቸውና ይህም ለውዝግብ መንስኤ መሆኑ ከስህተቶቹ መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የመሬት ምዝገባውና ሌሎች ተያያዥ ዝርዝር ጉዳዮች በመዝገብ ላይ በእጅ መጻፋቸው ምዝገባውን በየጊዜው ለማሻሻል ዕንቅፋት መሆኑ ይጠቀሳል፡፡

ከጥቂት ዓመታት በኋላ የተጀመረውና በአሁኑ ወቅት እየተከናወነ ያለው ሁለተኛው ዙር የመሬት ምዝገባና ማረጋገጫ እነዚህን ጉድለቶች ይፈታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ከአንደኛው ዙር በተለየ የሁለተኛው ዙር ምዝገባ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ከመጠቀሙ ባሻገር የመሬት መለኪያ እና የወሰን ማካለል ስራው የተሻለና አስተማማኝ ነው፡፡ እነዚህ ዝርዝር መረጃዎችም የምስክር ወረቀቱ አካል ናቸው፡፡ የመሬት ምዝገባውና በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዘ በመሆኑ በጊዜ ሂደት ለውጥ ካለ በዘመናዊ መንገድ አስፈላጊው ለውጥ ሊካሄድበት የሚችል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አሰራር ከፍተኛ ወጪና ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ፕሮግራሙን ከተጀመረ አስር ዓመት ቢያልፈውም በፕሮግራሙ እስካሁን መሸፈን የተቻለው ሰላሳ በመቶ (30%) የሆነው የእርሻ መሬት ብቻ ነው፡፡ ፕሮግራሙ የእንግሊዙን LIFT እና REILAን ጨምሮ ከግማሽ ደርዘን በላይ በሆኑ ለጋሾች የሚደገፍ ነው፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ገበሬው የመሬት ምዝገባ እና ማረጋገጫ ሰርተፊኬትን በመልካም ሁኔታ ቢቀበለውም ከእርሻና ከግጦሽ መሬቱ በመንግስትና በኢቨስተሮች ከመፈናቀል አልታደገውም፡፡ ይባስ ብሎም ከይዞታው በሚፈናቀልበት ወቅት የሚከፈለው ካሣ ለመሬቱ ሳይሆን በመሬቱ ላይ ላፈራው ንብረት ብቻ መሆኑ በመሬቱ ላይ ያለው የባለቤትነት መብት ጎደሎ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በሌላ በኩል ብዙ ጊዜ ሲነገር የማይሰማው የመሬት ምዝገባና ሠርተፊኬት መልካም ጎን ሴቶችን የመሬት ባለቤትነት መብት ማሳደጉ ነው፡፡ የመሬት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በባልና ሚስት ስም በጋራ የሚሰጥ ሲሆን፤ በዚህም መሬቱ በኪራይ፣ በእኩል እርሻ፣በጋብቻና ውርስ ስጦታዎች፣እና በመሳሰሉ ሌሎች የማስተላለፍ ውሳኔዎች ወቅት ባሎችና ዘመዶቻቸው ሊያማክሯቸው ይገደዳሉ፡፡ ፍቺ በሚኖርበት ጊዜም የመሬቱን ዕኩሌታ የማግኘት ህጋዊ መብት አግኝተዋል፡፡

## የመሬት ባለቤቶች ያጋጠሟቸው ተግዳሮቶች:-

አነስተኛ መሬት ባለቤት የሆኑ አርሶ አደሮች ካጋጠሟቸው ተግዳሮቶች መካከል የመጀመሪያው የመሬት ዕጥረት ነው፡፡ ለመሬት ዕጥረት ዋና ምክንያት እየጨመረ ያለው የሕዝብ ቁጥር ሲሆን በዚህ ሳቢያ መሬት ላይ ያለውጫና እየጨመረ መጥቷል፡፡ ከፍተኛ የሆነ የእርሻ መሬት ዕጥረት ችግርን ለመቅረፍ የግጦሽ መሬቶች፣ዳገታማ መሬቶች፣ ደኖች እና ሌሎች በቀላሉ የሚጎዱ ስነ ምህዳሮች ለእርሻ ስራ ውለዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በተለይ የሰሜን ደጋማ አካባቢዎች ከፍተኛ ለሆነ የአፈር መሸርሸርና የውሀ ምንጮች መድረቅ ለመሳሰሉ የስነ አካባቢያዊ መራቆት ተጋልጠዋል፡፡

ሁለተኛው ተግዳሮት የመሬት መከፋፈል/መበጣጠስ ነው፡፡ ይህም በዋናነት ባህላዊ በሆነው የውርስ ክፍፍል አንድ መሬት ለተለያዩ የቤተሰብ አባላት ሲከፋፈል የሚከሰት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ልማዳዊ የግብርና አሰራሮችም የመሬት መበጣጠስን ያስከትላሉ፡፡ ይህም የሆነው አርሶ አደሮች በመሬትለምነት ልዩነት ምክንያት አንድ ቦታ ሰፊ መሬት ከሚኖራቸው ይልቅ በተለያዩ ቦታዎች አነስተኛ መሬቶችን ለመያዝ ስለሚመርጡ ነው፡፡ በእነዚህ ድምር ምክንያቶች የተነሳ  የነፍስ ወከፍ ይዞታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ መጥተው የእህል ሰብል አምራች በሆኑ የሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች የአንድ ቤተሰብ ይዞታ ከአንድ ሔክታር በታች የደረሰ ሲሆን፣ የስር ሰብል (root crops) በሚያመርቱ የደቡብ ክልሎች ችግሩ ተባብሶ የነፍስ ወከፍ ይዞታ መጠን ከግማሽ ሔክታር በታች ሆኗል፡፡

ሦስተኛው ተግዳሮች በፍጥነት እየጨመረ የመጣው የመሬት አልባነት ችግር ነው:: በአንዳንድ አካባቢዎች መሬት አልባነት ከጠቅላላውን ማህበረሰብ ከሀያ እስከ ሀያ ስምንት በመቶ (20-28%) ደርሷል::መሬት አልባነት በቤተሰቦች፤ በማህበረሰብ ግንኙነቶች፤ በመሬትና ተያያዥ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጫና ያሳደረና የገጠር ድህነትና ስራ አጥነትን ያስከተለ ከፍተኛ ተግዳሮት ነው::

የመሬት አልባነት ዋነኛ ተጎጂዎች ወጣቶች ሲሆኑ የችግሩ አንዱ ውጤት ፍልሠትን ማስከተሉ ነው::መሬት አልባ ወጣቶች አካባቢያቸውን ለቀቀው በአገር ውስጥ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ወይም ድንበር በመሻገር ወደ ሌሎች ሀገሮች ለመፍለስ ይገደዳሉ:: ከአገር ውጪ የሚደረጉ ፍልሠቶች ብዙውን ጊዜ በህገ ወጥ መንገድ እና በህገወጥ አዘዋዋሪዎች እና የወንጀል ቡድኖች አማካኝነት እንደሚከናወን ይታመናል:: በተለያዩ መንገዶች ከሀገር ወጥተው በመካከለኛው ምስራቅ እና ደቡብ አፍሪካ ያሉ ህገ-ወጥ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ለስቃይ፣ ግድያ፣ ምዝበራ፣ እስር፣ የጥላቻ ጥቃቶች፣ ወሲባዊ ጥቃቶች እና ሌሎች በደሎች ተጋላጭ ሆነዋል::

ሌላው ገበሬዎች የገጠማቸው ተግዳሮቶች በይዞታቸው ላይ በመንግስትም ሆነ በግል ኢንቨስትመንቶች በሚያደርሱባቸው ጫናዎች ናቸው:: እንደመንገድ፤ የባቡር ሀዲዶች፣ የውሀኃይል ማመንጫዎች እና ሠፋፊ የቤት ልማት ፕሮጀክቶች የመሳሰሉ የመሠረተ-ልማት ፕሮጀክቶች ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት የሚፈልጉና ገበሬውን ከመሬቱ የሚያፈናቅሉ ናቸው:: ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የስኳር ልማት፣ የብረታብረትና ምህንድስና ኢንተርፕራይዞች፤ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች እና የመሳሰሉ ከፍተኛ የመንግስት ፕሮጀክቶች የገበሬውን መሬት ወስደዋል:: በተጨማሪም ለኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችና ለሰፋፊ እርሻ ልማቶች በሚል መንግስት የገበሬ መሬቶችን ለግል ባለሀብቶች ሰጥቷል::

ከዚህ በተጨማሪ በ1980ዎቹ መጨረሻ አካባቢ የተጀመረው የከተሞች በፍጥነት መስፋፋት በ2012 አካባቢ እስኪታገድ ድረስ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ከፍተኛ መጠን ያለው የእርሻና የግጦሽ መሬቶች ከገበሬዎች ወስዷል:: የነባር ከተሞች መስፋፋት በተጨማሪ በአውራ መንገዶች ዳር እና በገጠር አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ዙሪያም አዳዲስ ከተሞች እየተቆረቆሩ ነው:: እነዚህ ሁሉ ሂደቶች ገበሬው የእርሻ መሬቱን እንዲያጣና ከእርሻ ስራው ተፈናቅሎ ሌሎች የኑሮ አማራጮችን እንዲፈልግ አስገድደውታል::

## ማጠቃለያ

የመሬት ጥያቄ በኢትዮጵያ ዛሬም በሚገባ ምላሽ ያላገኘ ጉዳይ ነው:: ይሁን እንጂ ዛሬ ያለው የመሬት ጥያቄ ቀደም ሲል በ1950ዎቹ እና 1960ዎቹ ከነበሩት ጥያቄች በዓይነቱ እና በይዘቱ ይለያል:: ቀደም ሲል የነበሩት ጥያቄዎች ከሞላ ጎደል ምላሽ ተሰጥቷቸዋል:: ፍትሀዊ ባልሆነ መንገድ የመሬት ባለቤት የነበሩት የመሬት ከበርቴዎች እስከወዲያኛው ተወግደዋል፤ መሬትም ለአርሶ አደሮች ተከፋፍሏል:: ይሁን እንጂ ዛሬም መሬትን በሚመለከት አዳዲስ ጉዳዮች እና አዳዲስ ተግዳሮቶች ይታያሉ:: የመሬት ዕጥረት እና መበጣጠስ፣ መሬት አልባነት፣ የመሬት መሸርሸር፣ የመሬት ባለቤትነት መብት ደህንነት እንዲሁም መንግስት፣ ባለሀብቶችና ከተሞች የገበሬውን መሬት መንጠቅ ከመሬት ጋር የተያያዙ አሳሳቢ ችግሮች ሆነው መጥተዋል:: የገጠር ድህነት፤ የምግብ ዋስትና አለመኖርና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱም አደጋዎች ከመሬት ችግሮች ጋር የተያያዙና ምላሽ የሚሹ ጉዳዮች ሆነዋል::

ደሳለኝ ራህማቶ (ተመራማሪ)

ምንጭ:- ደሳለኝ ራህማቶ (2012) የገጠር መሬት ይዞታ በኢትዮጵያ - አጠቃላይ ግምገማ

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳብ የታተመው  የኦፐን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) የገንዘብ ድጋፍ ነው በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን የኦፐን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል::

§§ አድራሻ:- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS)    §§ ፖ.ሣ.ቁ.:- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

§§ ስልክ:- 011154 56 05/06 §§ ፋክስ:- 011154 56 07    §§ ኢሜል:- fss@ethionet.et §§ ድረ-ገጽ:- www.fssethiopia.org